Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# የወርቅ ማዕድን ቁፋሮና የበረታው ቅሬታ

## በኦሮሚያ ጉጂ ዞን በሚድሮክ እና በሳዱ የወርቅ ማዕድን ቁፋሮዎች ዙሪያ ያለው ውዝግብና ሥጋት

ይህ ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም የተጻፈው ‘የወርቅ ማዕድን ቁፋሮና የበረታው ቅሬታ፡ በጉጂ ኦሮምያ በሚድሮክ እና በሳዱ የወርቅ ማዕድን ቁፋሮዎች ዙሪያ ያለው ውዝግብና ሥጋት’ በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ሪፖርት ማጠቃለያ ትርጉም ነው። የሰላም ምርምር ተቋም በግጭት ምክንያቶችና አባባሾች እንዲሁመ ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃ የሚሰጥ ዕውቀት በማመንጨት በኢትዮጵያ ልሰላም ግንባታ ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚያደርግ ተቋም ነው። ተቋሙ የሚተዳደረው በስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም ሲሆን፣ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት በእንግሊዝ መንግሥት ነው።

አሰበ ረጋሳ እና ዳመና አበበ

# ማጠቃለያ

- በአገር አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ለውጥ ቢደረግም በኦሮሚያ ክልል በሚገኙት ሁለቱ የጉጂ ዞኖች (ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ) የማዕድን ቁፋሮ ሥራ የአካባቢውን ማኅበረሰቦች ማግለሉን ቀጥሏል። ይህ እውነታ በተለይ በሳውዑዲ ቢሊየነር ሼክ መሐመድ ሁሴን አል አሙዲ ባለቤትነት በሚተዳደረው የሚድሮክ የማዕድን እና የነዳጅ ኩባንያ ላይ ይስተዋላል።

- በብልጽግና ፓርቲ ወቅት የተቋቋሙ እንደ ጎዱ አጠቃላይ ትሬዲንግ አ.ማ. (GODU) ያሉ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች በ2010 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. በ2018) ሚድሮክ በክልሉ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን ውዝግብ ለማርገብ ወጣቶች እና የአካባቢው የንግድ ልሂቃን እንዲሳተፉ አድርጓል።

- በ2010 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. በ2018) የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እና የብልጽግና ፓርቲ ወደ ሥልጣን መምጣት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ አዳዲስ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ተዋናዮችን አፍርቷል። ይህም በኦሮሚያ ክልል ወርቅ ለማውጣት የሚሰጠውን ፈቃድ ቁጥር ከፍ እንዲል ምክንያት ከመሆነ ባለፈ፣ በተለይ በጉጂ ዞኖች አዲስ የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ ሽሚያ እንዲፈጠር አድርጓል።
- ይሁን እንጂ በአንዳንድ አዲስ የማዕድን ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ታይቷል። እ.ኤ.አ. ከ2018 ጀምሮ መንግሥት አስራሩን ተቃዋሚዎቹን ከመጠምዘዝ፣ በግዳጅ መሬት መንጠቅን ጨምሮ ወደ ጉልበትና የጭቆና እርምጃዎች ቀይሯል ።

- የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ቁፋሮ በሰዎች እና በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ተከትሎ በተፈጠረው ተቃውሞ መንግሥት በግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. የኩባንያውን ፈቃድ አግዶ ነበር። የተቃውሞው ዋና ዋና መንስኤዎች ሳይታረሙ የማዕድን ቁፋሮው በመጋቢት ወር 2013 ዓ.ም. እንደገና እንዲከፈት ተፈቅዶለታል። ይልቁንም የሚድሮክ ቦታ የሆነውን የአኮቴ ማዕድን ወደ ጎዱ (GODU) በማዛወር በአካባቢው ልሂቃንን እና ነጋዴዎች የሚድሮክን ፈቃድ መታደስ እንዳይቃወሙ ለማድረግ ተሞክሯል።

- ግልጽ የሆነ የማኅበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ ባለመኖሩ እና የማዕድን ቁፋሮ ሥራው በአንጻራዊነት በቅርብ ጊዜ በመጀመሩ እንደ ጎዱ (GODU) ያሉ አዲስ የተቋቋሙ ኩባንያዎች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎቻቸው ገና ግልፅ አይደሉም። ነገር ግን የአካባቢው ማኅበረሰብ በሚድሮክ ላይ ያለው ቅሬታ በተጨባጭ የሚታይ ነው።

- መንግሥት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያመቻቹ ሥልቶችን ካልቀየሰ በቀር በአካባቢው የሚነሱ ቅሬታዎች በማዕድን ቁፋሮ ላይ እንደገና ተቃውሞ ሊቀስቅሱ ይችላሉ። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የማኅበረሰቡ የጋራ ተጠቃሚነት፣ በቂ ካሳ፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎች እንዲሁም ከማዕድን ቁፋሮው በፊት ቁፋሮው የሚያስከትላቸውን የአካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች ከአካባቢው ማኅበረሰቦች ጋር በመመካከር ከስምምነት መድርስ ናቸው።